# ልጅዎ ኩራት ነው

ከዘውዲቱ የማነ

2019-11-10



የ አሳምነው እናት፣ እጅጉን አዝነዋል
ሟ ች ልጅን ስላጡ፣ ይኸው ተጎድተዋል
ች ለው አልተፅናኑም፣ ተክዷል አውቀዋል።
ጀ ነራል ነበረ፣ ልጁ የጦር መሪ
ነ ጥለው አጠቁት፣ አድረው ለመሰሪ።
ራ ዕይ ነበረው፣ የድህው ጠበቃ ።
ል በ ሰፊው ጀግና፣ ለድል የሚያበቃ።
እ ውስጣቸው ገብቶ፣ የእናቲቱ ሀዘን
ና ፍቀው ወየው ልጀ፣ በመጦሪያቸው ቀን
ት ካዜቸው ያማል፣ ይሆናል ሰቀቀን።
አ ስራትን ያጠፉ፣ ደግሞ አሳምነውን
ን ቁ ጀግኖቻችን፣ በሸፍጥ ተለዩን።
ገ ዳዮቻችንን፣ ቀድመው የሚያነቡ
ት ንፋሻቸው ጠፋ፣ በሰበብ በአስባቡ።
መ ሞትም ክብር ነው፣ ላመኑበት ነገር
ድ ንግዝግዝ ያለውም፣ ይጠራል እያደር
ፋ ኖ ተጠናከር፣ መብት ለማስከበር
ት ጥቅ ያስፈልገናል፣ ጀግናው ብሎን ነበር።
ል ምጥምጥ ነውና፣ አዴፓ ሲፈጠር
ብ ልሁ ሲያሳስብ፣ መች አለው ቁምነገር!
ይ ነገር አቋሙ፣ እንመስክር ሁላችን
ሰ ይጣን ቀማን እንጅ፣ ጀግና ነው ልጃችን
ብ ርጋዴል ጀነራል፣ ሁሌም ኩራታችን
ራ ሱን የሰዋው፣ ለአማራነታችን
ል ጅዎ ኩራት ነው፣ ይበርቱ እናታችን።